# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 5 ቁጥር 4 ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ.ም.

## የሜይ ዴይ ሰማዕታት

በኢትዮጵያ ሀገራችን በተለያየ ጊዜ የፈሰሰ የልጆቿና የጀግኖቿ ደም በታሪክ ይታወስ፣ ይወሳ ዘንድ መዘከር አግባብነት አለውና ዛሬም 41 ዓመት መለስ ብለን እናስታውሳለን። የዐድዋ፣ የማይጨው፣ የየካቲት 12፣ እያልን የሰማዕታትን ተጋድሎ ስንዘክር ሀገር ለልጆቿና ለጀግኖቿ ክብር እንድትሰጥ ነው። በስም ዓፄ ቴዎድሮስ፣ ዓፄ ዮሐንስ አቡነ ጴጥሮስ፣ ወዘተ እያልን መስዋዕትነታቸውን ስንተርክ ኢትዮጵያ ለክብሯ ነገስታት፣ የሃይማኖት አባቶች፣ አርበኞች ሳይቀሩ እንደተሰዉላት ለመዘከር ብቻ ሳይሆን የነሱን አርአያ መከተል ለሀገርና ሕዝብ ክብር ነውና ነው። ለሀገርና ሕዝብ መስዋዕት መሆን በታሪክ ክብር ቦታ እንዳለው ለማስገንዘብ ነው። ሀገር አለሁልሽ የሚላት፣ ከራሱ በፊት ኢትዮጵያዬ የሚላት ትውልድ ይተካ ዘንድ የቀደሙትን መዘከር አግባብ ነው። ለመብትና ነጻነት የሚደረግ ትግል ሕይወት ፈላጊ ነው። በትግል ሜዳ የወደቁ ወገኖቻችን በመዘከር ዳግም ታጋይ ይበቅልባት ዘንድ፣ አለሁልሽ ባይ ሀገር ትወልድ ዘንድ ትምህርት ቤቱ ከታሪክ ማህደር ነውና ያለፈውን ሳንዘነጋ ለነገው እንዘጋጅ ዘንድ በየቦታው የወደቁ ወገኖቻችንን እንዘክራለን።

ለመብትና ለነፃነት የሚከፈል መስዋዕትነት ድልን ሲያስመዘግብ የፈሰሰው ደም ሁሳ ሀገር ያለመልማል። የተከሰከሰው አጥንት የሀገር ዳር ድምበር አጥር ይሆናል። ሀገር በልጆቿ ጀግንነት ትኮራለች። ሲጻፍላቸው፣ ሲዘፈንላቸው፣ ሲገጠምላቸው፣ ሲፎከርላቸው፣ ሲሸለልላቸው እውንም ያምራል። በከፈሉት መስዋዕትነት ሀገርንና ሕዝብን ከወራሪ ጠላት፣ ከቅኝ አገዛዝ ቀምበር አላቀዋልና ትውልድ ይኮራባቸዋል። ክብርና ምስጋና ለዛሬ ላበቁን እያልን በየዓመቱ ስንዘክራቸው በኩራት ነው። ኢትዮጵያዊነት አትንኩኝ ባይነት ስንል ጀግኖቻችን ስላሳሳፈሩን ነው። ከድሉ ጫፍ ላይ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ስላውለበለቡልን ነው።

ሕይወት ያለ ፍሬ፣ ደም ያለ ድል ሲቀጠፍ፣ ሲፈስ ትርፉ ቁጭት ቢሆንም የጀግና ትውልድ ጀግንነትን ከፍ አድርገን እናደምቃለን። በመላዋ ኢትዮጵያ የዛሬ 41 ዓመት የዓለም ሠራተኞችን ቀን (ሜይ ዴይ) ምክንያት በማድረግ ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. ከምሽቱ 12 ሰዓት ገደማ ጀምሮ በአዲስ አበባና በመላዋ ኢትዮጵያ የፈሰሰውን በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ደም “የሜይ ዴይ ሰማዕታት” ብለን እንዘክራቸዋለን፣ እናስታውሳቸዋለን። የትግላቸው ክንድ ላብ አደሩ ነበርና ለላብ አደሩ በዓል ብሶቱን ይዘው አደባባይ የወጡ ወጣቶች ገና ሳይንቀሳቀሱ የፋሽስት ደርግ ቢ. አርና ክላሽ ተርከፈከፈባቸው። “ሜይ ዴይ የትግላችን ቀን ነው!” ብለው ሳይጨርሱ የደማቸው ቀን ሆነ።

እነሆ! «ያ ትውልድ ተቋም» ለሜይ ዴይ ሰማዕታት ያለንንን ክብርና ሞገስ እየገለጽን በመላ ኢትዮጵያና በመላው ዓለም ላላችሁ ለቀይ ሽብር ሰለባ ቤተሰቦችና ወገኖች መጽናናቱንና ብርታቱን

ይስጣችሁ እንላለን። ጊዜ ለሜይ ዴይና ለቀይ ሽብር ሰማዕታት አልቀመምና አልቅሳችሁ ላልወጣላችሁ ቤተሰቦች፣ ስለ ልጆቻችሁ ተናግራችሁ ያልረካችሁ ወገኖች አሁንም ጥንካሬውን ይስጣችሁ እንላለን። ነገ ብሩህ ቀን ይመጣልና ትውልድ ሲዘክራቸው እንደሚኖር ተስፋችንን ልናስቀምጥ ወደድን።

«ያ ትውልድ ተቋም» በዛሬው እትማችን ከዚህ በፊት ስለ ሜይ ዴይ 1969 እና ቀይ ሽብር ሰማዕታት ካስነበብናቸው ህያውነት አላቸው የምንላቸውን አገላለጾች በመንተራስ 41ኛ ዓመት የሜይ ዴይ ሰማዕታትን እንዘክራለን።

"ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. ከምሽቱ 1:00 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ በአራቱም አቅጣጫ የተኩስ ድምጽ አልፎ አልፎ ማስተጋባቱ ታውቋል።...በ22/8/69 ጠዋት ባደረግነው መከታተል...በቀጨኔ መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን አካባቢ የ31 ተማሪዎች አስከሬን፣ በየካ ወረዳ አሥመራ መንገድ የ42 ተማሪዎች አስከሬን ወድቆ መገኘቱና በአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ አንሽነት ተለቅሞ ወደ ምኒልክ ሆስፒታል መወሰዱን...በ23/8/69 እንደዚሁ በገፈርሳ ወረዳ ሳንሱሲ ከሚባለው አካባቢ የ19 ተማሪዎች አስከሬን በጫካ ውስጥ ተጥሎ በአካባቢው ሕዝብ ስለተገኘ...በ24/8/69 በየካ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የ22 ተማሪዎች አስከሬን ተቀብሮ መዋሉን...ይህን መሰል ድርጊት የተፈጸመው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በክፍለ ሀገራትም ጭምር መሆኑንም ተጨማሪ መረጃ ደርሶናል።"

"አምቡላንስ መኪና በሽተኛ ማመላለሱ ቀርቶ በቀይ ሽብር ምክንያት የተገደሉትን ሰዎች እያነሳን ወደ ቀብር ቦታ መውሰድ ጀመርን።...ስንደርስ በጥይት የተመታ በላዩ ላይ "ነጭ ሽብር በቀይ ሽብር ይመታል" የሚል ፅሁፍ የተለጠፈበት አስከሬን እናገኛለን። በከተማው ውስጥ በተለያየ ቦታ ላይ ተጥሎ የሚገኝ ሲሆን የሚበዛው መርካቶ፣ ፒያሳ፣ አንበሳ ጋራዥ፣ አካባቢ ነበር። ደርግ ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ ገብተን አስከሬን እናወጣ ነበር። አብዛኛዎቹ እጃቸው ታስሮ ነበር የሚገኙት።...በየከተማው የወደቁትን የምናነሳው ለሊትና በጠዋት ነው። የተወሰነ ጊዜ አስከሬናቸውን ሰው ይመልከተው ተብሎ እስከ ቀኑ 3:00 እና 4:00 ሰዓት ድረስ ከቆየ በኋላ የሚነሳበት ጊዜ ነበር።...አስከሬኑን ካነሳን በኋላ ለመቅበር ጴጥሮስ ጳውሎስ ቤተክርስቲያን እንወስዳለን።...በዚህ ሬሣ ማንሳት ሥራ ላይ እስከ 1970 ዓ.ም. ድረስ ለአንድ ዓመት ያህል ሰርቻለሁ።..."

"በየመንገዱ ሰው መገደል ሲጀምር ማለት በቀይ ሽብር መንግስት ሰውን ሲገድል ማለቴ ነው፡ በዛን ጊዜ ዕረፍት አልነበረንም። ቀን ተሌት ከየከፍተኛው፣ ከቀበሌው፣ ከቤተመንግስት፣ ከየፖሊስ ጣቢያው ከየመንገዱ ከየቦታው ማንሳት ነው።...ሰው በየቀኑ ስለሚገደል ጉድጓድ ቆፋሪ ሰራተኞች...ጎጆ ሰርተው ሲቆፍሩ ውለው እዛው ያድራሉ።...በዛን ጊዜ 24 ሰዓት ሙሉ ምግብ የማንበላበት ጊዜ ነበር።"

"...አንዳንድ ሰዎች በተፈላጊነት እየተጠሩ ከመኖሪያ ቤታቸው ከተወሰዱ በኋላ በማግስቱ አስከሬናቸው የተገኘ አሉ።...አንዳንድ ቤተሰቦች ሬሳውን ፈልገው ካገኙ በኋላ አስከሬኑን ለመቅበር የተጠየቀውን ገንዘብ ከፍለው የሬሳ ሣጥንም ገዝተው ለመቅበር ሲዘጋጁ ተከልክለዋል።"

"ምኒልክ ሆስፒታል አስከሬን ምርመራ ክፍል እሰራለሁ። በአዲስ አበባ ከተማ በቀይ ሽብር ወጣቶች በሚገደሉበት ወቅት ...የአስከሬኑ ብዛት...መናገር አልችልም። ከምድር አንስቶ እስከ ጣራ ድረስ አስከሬን በአስከሬን ላይ ተከምሮ የሚቾቹ ቤተሰቦችም በአስከሬኑ ላይ እየቆሙ ልጆቻቸውን ሲፈልጉ አይቻለሁ።"

"አስከሬን ናቸው ተብለው ከመጡት መካከል ጥቂቶቹ ህይወት እየዘሩ ውሃ! ውሃ! አድኑኝ! በማለትና ሌላም ነገር በመናገር ይለፈልፋሉ።...አንዲት ቀይ ቀጠን ያለች 20 ዓመት የሚሆናትና አንድ ጠይም 20-25 ዓመት የሚሆነው ወጣት...አድኑኝ! ውሃ! ውሃ! ሲሉ ነበር። በተለይ ሴቷ ዶ/ር ፍቅሬን ጥሩልኝ አድኑኝ እያለች ትናገር ነበር።" «ደም ያዘለ ዶሴ» የልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት፤ ጥር 2002 አዲስ አበባ።

የዛሬ 41 ዓመት አርብ ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. በመላዋ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርት (ኢሕአፓ) ዓለም አቀፍ የሠራተኞችን ቀን፡ ሜይ ዴይ ምክንያት በማድረግ አባላቱና ደጋፊዎቹ በየአካባቢያቸው በሰላማዊ ሰልፍ የተነሱበትን ዓላማ በማስተጋባት የትግል አንድነታቸውን ለመግለጽ ከምሽቱ 12:00 ሰዓት ጀምሮ ለሰልፍ ተንቀሳቀሱ።

ደርግ ብ/ጄ ተፈሪ ባንቴንና ወደ ስድስት የሚጠጉ የደርግ አባላትን በፋሽስቱ መንግሥቱ ኃይለማርያም አቀናባሪነት ጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም. ከረሸነ በኋላ በተለይ በኢሕአፓ ጥላ ሥር የተሰለፉ፡ የደገፉ፡ ያዩ፡ ያለፉትን ከሕፃናት እስከ አዛውንት ደም በማፍሰስ የበላይነቱን ለማረጋገጥ "አብዮታችን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋገረ"፣ "ለምሳ ያሰቡንን ለቁርስ አደረግናቸው" ፉከራውን ቀጠለ። ይህንንም ፉከራውን ተግባራዊ ለማድረግ ሚያዝያ 6 ቀን 1969 ዓ.ም. ደም የተሞላ ጠርሙስ "በአብዮት" አደባብይ በመስበር የቀይ ሽብር ቅድመ ዝግጅት "ነፃ እርምጃ" በመላዋ ሀገሪቷ በተለይ በአዲስ አበባና በተለያዩ የገጠር ከተሞች ጭምር የበርካታዎችን ሕይወት በየደቂቃው እየነጠቀ ያለፈበት ፋሽስታዊ ወቅት ነበር።

ዓለም አቀፍ የላብ አደሩን ቀን ሜይ ዴይ 1969 ዓ.ም. ከደርግ ልቅ ያጣ አፈናና ጭፍጨፋ አንፃር በዕለቱ ማክበር እንደማይቻል የተገነዘበው ኢሕአፓ፡ ሁለት ቀናት ቀደም ብሎ ለኢትዮጵያ ሀገሩና ለጭቁን ሕዝቦች ያለውን ታማኝነትና የዓላማ ጽናትና ቆራጥነት ለማረጋገጥ የተዘጋጀው የሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. ሰልፍ ከድርጅቱ እየከዱ ወደ ደርግ መግባት በጀመሩ አንጃዎች ሙሉ መረጃ ለደርግ በመድረሱ መንግሥቱ ኃይለማርያምና ጀሌዎቹ አብዮት አደባባይ በምሳሌነት ያፈሰሱትን ደም ሊጠጡ ቋምጠውና አድፍጠው ተጠባበቁ።

ሰልፉ ሲጀመርና የጥይት ሩምታ ሲለቀቅ እኩል ሆነ። በርካታ ሕፃናትና ወጣቶች "ፍጹም ነው እምነቴ" እንዳሉ ሕይወታቸውን ለትግሉ ሰጡ። አዲስ አበባ የደም ጐርፍ አጥለቀለቃት። በየአካባቢው ምሽቱ ደም በጠማቸው የደርግ ገዳዮች ሽብር ሆነ። ማ ይሙት ማ ይትረፍ መለየት እስኪያቅት ተኩስና ለቅሶ ለሊቱን አድረውበት፡ ለተረኛው ንጋት ለቀቁ። ነጠላዎች ተዘቀዘቁ፡ ቀሚሶች ጥቁር ሆኑ፡ እናቶች አባቶች ሀዘን፡ ቁጭትና እየዬ ዋጣቸው። አስፋልቶች በወጣቶች ደም ታጠቡ። ልክ የዛሬ 41 ዓመት። ሜይ ዴይ ሊዘከር የሚገባው በልጆቻችን ደም የተከበረ የዓለም ሠራተኞች ቀን።

ደርግ አንድ ብርቅዬ ትውልድ ጨረሰ። ሀገሪቷ በድህነት አቅሟ ለልማትና ለዕድገት የኮተኮተቻቸው ልጆቿን ደርግ በላ። ለሕዝብ መብትና ነፃነት በግምባር ቀደምትነት የተሰለፉ ጀግኖች ልጆቿን፤ እምቡጥ አበባዎቿን ኢትዮጵያ ተነጠቀች። ኢትዮጵያዊነት ኩራቷን መለያ ክብሯን ጥቁር ድባብ አጠላባት። እምቢኝ ለመብቴ፤ እምቢኝ ለሀገሬ፡ እምቢኝ ለሕዝቤ ያለ ትውልድ በጥይት ተለቀመ። እየታነቁ ተገደሉ። በቁማቸው ከገደል አፋፍ ተወረወሩ። ወደ ባህር ተጣሉ። ሕጻናት ይህን አረመኔያዊ ድርጊት እያዩ እንዲያድጉ ተደረገ። የዚህ አረመኔ አገዛዝ ጠስ ለዛሬም ተርፎ ብሔራዊ ስሜት እተሸረሸረበት፤ የአባት የእናቶቻችን ጀግንነት ተረት ተረት እሆነበት ጊዜ ላይ አድርሶናል።

«ያ ትውልድ ተቋም» ልክ የዛሬ ስድስት ዓመት ለሀገራቸው ክብርና ለሕዝባቸው መብት ሲፋለሙ ክቡር ሕይወታቸውን ለሰዉት የኢትዮጵያ ጀግኖችና የያ ትውልድ ሰማዕታት መታሰቢያነት በያ ትውልድ ስም ያ ትውልድ ድረ ገጽን (www.yatewlid.com www.yatewlid.org) ለሕዝብ ይፋ ማድረጋችን ይታወቃል። ለሜይ ዴይና ለቀይ ሽብር ሰማዕታት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የያ ትውልድ ድረ ገጽ ይፋ የሆነበትን ሚያዝያ 23 ቀን 2004 ዓ.ም. ስድስተኛ ዓመት ስናከብር ታሪካችን ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፍ ዘንድ በሩን ስንከፍት በታላቅ ደስታ ነው። ዛሬ አጠገባችን የሌሉትን ወንድምና እህቶቻችንን ቢያንስ ስማቸውንና ምስላቸውን እንደያዘ ሚተላለፍ በየትም ሀገርና

ቦታ ሆነው የሚያዩት ሐውልት አቁመንላቸዋልና ከተቀበልነው አደራ ጠብታዋን በማድረጋችን፡ በመጀመራችን እየተደሰትን ከፊታችን የተደቀነውን ከባድ ኃላፊነት በትጋትና በሙሉ ስሜት ለመወጣት ቃል በመግባት ነው።

አብረን ተሰልፈን፡ አብረን ጮኸን፡ አብረን ታግለን፡ አብረን ተሰቃይተን በተለያየ አጋጣሚ ዛሬ በሕይወት ያለን የዚያ ትውልድ አባላት ቢያንስ ልንዘክራቸው፡ ልናስባቸው ይገባል። እኛ ልንኖር እነሱ ሞተዋል። ሕይወታቸውን ለኢትዮጵያ አድርገው ተሰውተዋል። ሕይወታቸውን ለሕዝብ ዝማሬ ሰጥተዋል። ደማቸውን ያፈሰሱ አጥንታቸውን የከሰከሱት "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም" "የዴሞክራሲ መብት ያለገደብ ለሁሉም" እየፈከሩ፡ "ደሀ ደሀ ምን ታየበት፤ እንዳይማር የሆነበት" እየዘመሩ፡ ለሕዝብና ለሀገር እንደጮሁ፡ መሆኑን በመመስከር ታሪካቸው ታሪካችን፡ ደማቸው ደማችን ነውና፡ እነሱን እያስታወስን አኩሪ ተጋድሏችንን ከታሪክ በራዦችና ጥላሸት ቀቢዎች በመጠበቅና በመከላከል ቀጣዩ አዲስ ትውልድ እነማን እንደነበርንና ምን ሠርተን እንዳለፍን ግንዛቤ በማስጨበጥ ከእኛ ሊቀስም ከሚችለው ትምህርት በመውሰድ ሀገሩንና ሕዝቡን አፍቃሪ ብቁ ዜጋ ይሆን ዘንድ ማዘጋጀት ይጠበቅብናል።

«ያ ትውልድ ተቋም» የዛሬ ስድስት ዓመት ማለትም ሚያዝያ 21 ቀን 2004 ዓ.ም. (April 29, 2012) ለያ ትውልድ ቀይ ሽብር ሰማዕታት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ለሕዝብ ይፋ ያደረግነውን ድረ ገጽ ከሜይ ዴይ ሰማዕታት ጋር ስናስተዋውቅ በዚህ ሁኔታ ነበር፦

"የዚያን ትውልድ ታሪክ ማሰባሰብና ለታሪክ ተመራማሪዎች፡ ፀሀፊዎችና ለተተኪው ትውልድ ማስረከብ አንዱ ተልዕኮው አድርጎ የተነሳው የዚያ ትውልድ አካል የዛሬን ቀን በማስታወስ ለሀገራቸው ሉዓላዊነትና ለሕዝባቸው ክብር ሲሉ በተለያዩ አገዛዞች መስዋትነት ለከፈሉና እየከፈሉ ላሉ እንዲሁም በኢሕአፓ ጥላ ሥር ተሰልፈው በትውልድ መመተር ቀይ ሽብርና ነፃ እርምጃ ለወደቁት ወገኖቻችን መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ያ ትውልድ ድረ ገጽ www.yatewlid.com, www.yatewlid.com, ከዛሬ ሚያዝያ 21 ቀን 2004 ዓ.ም. (April 29, 2012) ጀምሮ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አበርክተናል።"

በዚህ መልኩ የተንቀሳቀሰውና ሰኔ 28 ቀን 2004 ዓ.ም. መሥራች ጉባኤውን በዳላስ ያደረገው «ያ ትውልድ ተቋም» በስድስት ዓመት ጥረታችን ድረ ገጹ የእንግሊዘኛ ክፍል እንዲኖረው በማድረግና ያልተካተቱ በርካታ ሠነዶችን በማካተት በአዲስ መልክ አዘጋጅተነዋል። በተጨማሪም www.yatewlid.com, www.yatewlid.com, ድረ ገጽ www.redterror.org, www.thatgeneration.org ድረ ገጾች የድረ ገጹ መግቢያዎች ይሆኑ ዘንድ እንደሚያገለግሉ ስናሳውቅ በታላቅ ደስታ ነው።

ውድ የኢትዮጵያ ልጆችና ሕዝባችን! ከጎናችን ሳትለዩ ላበረታታችሁን የያ ትውልድ ወገኖችና አካላት፤ በተለያየ ወቅት ትብብር ላደረጋችሁልን የሚዲያ፤ የድረ ገጽ ወገኖችና በጠንካራ መሰረት በመሰባሰብ እዚህ ላደረሳችሁት የ«ያ ትውልድ ተቋም» አባላት በሞላ የዓለም ሠራተኞችን ቀን ሜይ ዴይ 2004 ዓ.ም.ን ምክንያት በማድረግ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ ላደረግነው ያ ትውልድ ድረ ገጽ ስድስተኛ ዓመት ክብረ በዓልና ዝክረ ሰማዕታት ቀናችን እንኳን በደህና አደረሳችሁ እንላለን።

በተጨማሪም በሜይ ዴይ 1969 ዓ.ም. በመላዋ ኢትዮጵያ በሰላማዊ ሰልፍ የሕዝባቸውን ብሶት ሊያሰሙ በወጡ የሕዝብና የኢሕአፓ ልጆች ላይ በተደረገው አስከፊ፣ ዘግናኝና አረመኔአዊ ግድያ ለተሰዉ ወገኖቻችን በሙሉ ክብር ለናንተ እያልን ለቤተሰቦቻቸው፣ ለዘመድ አዝማድና ለትግል ጓዶቻቸው ጭምር ብርታትና ጥንካሬ አይለያችሁ ስንል ከ«ያ ትውልድ ተቋም» ድምጻችንን እናሰማለን።

**ያ ትውልድ ተቋምን በመተባበር የመረጃ ምንጭ ይሁኑ!!!**

**ክብር ለቀይ ሽብርና ለሜይ ዴይ ሰማዕታት!!!**

***«ያ ትውልድ ተቋም»***


**ሚያዝያ** 21 **ቀን** 2010 **ዓ.ም.** (May Day 2018)

Email : yatewlid@yahoo.com, yatewlid@gmail.com,

**ምሥለ ገጽ** (Facebook) ፡ yatewlid

**ስልክ ፡** (703) 300 4302 **ወይም** (615) 306 4164

website : http://www.yatewlid.com , http://www.yatewlid.org

http://www.redterror.org , http://www.thatgeneration.org